# <u>ጥናት አንድ የዳንኤል መግቢያ ጥናት (ለመሪው የተዘጋጀ)</u>

1. ኢየሱስ ክርስቶስ በማቴ 24፡15-16 ላይ የዳንኤልን ትንቢት አስመልክቶ የተናገረው ንግግር ለመጽሃፉ ያለውን አመለካከት ያስረዳናል፡፡
2. ይህ አነጋገር የሚያስረዳን የዳንኤል መጽሃፍ ዝም ብለን ለማንበብ ያህል ብቻ ገረፍ አድርገን የምናልፈው ሳይሆን በማስተዋል ጊዜአችንን ወስደን የምናጠናው ነገር እንደሆነ ከጌታችን አነጋገር እንረዳለን፡፡
3. ዳንኤል ያገለገለው በአራት ነገስታት ዘመን ሲሆን፤ እነርሱም፡ 1) ናቡከደነጾር ዳን 1፡1 2) ቤልሻዛር ዳን 5፡1 3) ዳርዮስ ዳን 6፡1 እና 4) ንጉስ ቂሮስ ዳን 1፡1 እና 10፡1 ናቸው፡፡ የነገስታት መቀያየር፣ ክፉ ሆነ መልካም ንጉስ መቀመጡ ለዳንኤል ህይወት ምንም ለውጥ አልነበረውም፤ ማለትም ታማኝነቱን ለአምላኩ ብቻ ሳይሆን ለነገስታቱም ጠብቋል ስለዚህም በአህዛብ መሃል በሁሉም ተከብሮና አምላኩን አክብሮ መቆየቱ ህይወታችንን መለስ ብለን እንድናይ ያስገድደናል፡፡
4. ትምህርት አለው እላለሁ፤ ይህም ሰው ሁልጊዜ ራሱን ሲያይ እንደጥሩ፣ መልካምና በጎ ምግባር ያለው እንደሆነ አድርጎ ይመለከታል፤ ሆኖም እግዚአብሄር ሰዎችን ሲመለከት ግን በኤር 17፡9 ላይ እንደሚናገረው ክፉትና ተንኮል የሞላበት ከአውሬ የባሰ እንደሆነ ይታያል፡፡
5. ይህ ማለት እስራኤል ከዳዊት ዘር የሆነ ንጉስ በዙፋን ላይ ሳይኖር የአህዛብ መንግሥታት በተለያየ መንገድ የሚገዙበት ሲሆን፤ ይህም የጀመረው በመጀመሪያው የይሁዳ ምርኮኞችና ንጉሳቸው ወደ ባቢሎን ሲወሰዱ ማለትም በ605 ዓ.ዓ ነው፡፡ ይህ በአህዛብ መገዛት የሚያበቃው ኢየሱስ መጥቶ የአህዛብን መንግስታት በመደምሰስ የራሱን መንግሥት ሲያቋቁም ይሆናል፡፡

<u>ተጨማሪ ሃሳቦች</u>

- ናቡከደነጾር በ605 የመጀመሪያዎቹን ምርኮኞች ወሰደ 2ኛ ነገስት 24፡1-4
- የዳንኤል መጽሃፍ ባይኖር ራዕይንና በአጠቃላይ ትንቢትን ለመረዳት አስቸጋሪ ይሆን ነበረ፡፡
- የዳንኤል አገልግሎት በ597 ወደ ባቢሎን ከተወሰደው ከህዝቅኤል አገልግሎት ጋራ ጊዜው ይገናኛል፡፡ ህዝቅኤል ስለዚህ ወጣት ነብይ ያውቅ ነበረ፡፡ ህዝ 14፡14፣ 14፡20፣ 18፡3
- ዳንኤል ወደ ሃገሩ ወደ ይሁዳ እንደተመለሰና እንዳልተመለሰ የሚናገር መረጃ የለንም፡፡
- የመጽሃፉ ጸሃፊ ዳንኤል እንደሆነ በዳን 8፡1፣ 9፡2፣ 10፡2 እና በማቴ 24፡15 እናገኛለን፡፡
- የዳንኤል ትንቢት የተጻፈበት ቢያንስ ሁለት ዋና አላማዎች ሲኖሩት እነዚህም፡ የመጀመሪያው በዳን 5፡21 ላይ እንደምናየው እግዚአብሄር በሰው ልጆችና ሁኔታዎች ላይ ሁሉ ሉዓላዊነት እንዳለው ለአህዛብ ለማብሰርና ለአይሁድ ደግሞ ለማስታወስ ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ በሞትና በህይወት መሃል ለአምላካቸው ለእግዚአብሄር በምሳሌነት የሚቆሙ ሰዎች እንዳሉት በማሳየት ለተቀረው በባቢሎን ለሚኖረው የአይሁድ ህዝብ ምሳሌ እንዲሆን፡፡
- በዳን 9፡25-26 ‹‹መሲህ›› የሚለው በብሉይ ኪዳን በዳንኤል መጽሃፍ ብቻ ይታያል፡፡
- ዳን 7፡13 ‹‹የሰው ልጅ›› ብሎ መሲሁን መጥራት በዚህ ክፍል ብቻ ይገኛል፡፡ ህዝቅኤል ይህንን ቃል በብዛት ተጠቅሟል፤ ነገር ግን ለመሲሁ ሳይሆን ስለራሱ ሲናገር ብቻ ነው፡፡
- ቅዱሳን መላዕክትን በስማቸው የጠራ በብሉይ ኪዳን ዳንኤል ብቻ ነው፡፡ ዳን 8፡16፣ 9፡21፣ 10፡13፣ 10፡21 በመጽሃፍ ቅዱስ ባጠቃላይ ከመላዕክት ሚካኤልና ገብርኤል ብቻ ናቸው በስም የተጠሩት፡፡
- ኤር ምዕራፍ 27ትን በአጠቃላይ ስንመለከት የአይሁድ በባቢሎን እጅ መውደቅ የእግዚአብሄር ፈቃድ መሆኑን ኤርሚያስ በሚገባ ተገንዝቧል፡፡

# ጥናት ሁለት ዳን 1፡1-10 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ኢየሩሳሌምን የከበበው ንጉስ ስሙ ናቡከደነጾር ይባላል፡፡ ኢየሩሳሌም ስትከበብ ንጉስ የነበረው ሰው ኢዮአቄም ይባል ነበረ፡፡
2. የይሁዳ ወደ ምርኮ መወሰድ በእርግጠኛነት መናገር የምንችለው ነገር፤ እግዚአብሄር ራሱ ይሁዳን አሳልፎ የሰጠ እንጂ የባቢሎን ንጉስ ሃይልና ብርታት ይህንን እንዳላደረገ መረዳት ይቻላል፡፡ በዚህ ሁሉ የምናሴ አስተዋጽኦ ከሁሉ በላይ በጊዜው ንጉሥ አድርጎ የሾመው ሰውና ህዝቡን በጽድቅ ሊያስተዳድር ሲገባው በሃጥያት መበከሉ ለህዝቡም የጥፋት መንገድ ሆኖአል፡፡
3. ይህም ቁጥር እንደ 2ኛ ነገ 24፡1-4 ይሁዳን ለምርኮ የሰጠው እግዚአብሄር ራሱ እንደሆነ ያረጋግጣል፡፡ ዘዳግም ውስጥ ያሉትን ክፍሎች ስናነብ እግዚአብሄር ቢታዘዙ በረከትን ቃል እንደገባ፤ ባይታዘዙ ደግሞ የሚገጥማቸውን ስለተናገረ ያንኑ የተናገራቸውን ቃል ነው ሲፈጽም የምናየው፡፡
4. አስፋኔዝ የተባለው የጃንደረቦች አለቃ የታዘዘው ነገር ከንጉሳዊ ቤተሰብና ከመሳፍንት ዘር የሆኑትን እስራኤላውያን እንዲያመጣ ነበረ፡፡ ሚዛኖቹ፡ 1) የአካል ጉዳት የሌለባቸው 2) መልከ መልካሞች 3) ማንኛውንም ትምህርት የመማር ችሎታ ያላቸው 4) እውቀት የሞላባቸው 5) ሁሉን በፍጥነት መረዳት የሚችሉ 6) በንጉስ ቤት ለማገልገል ብቃት ያላቸው 7) ወጣቶች 8) ወንዶች የሚሉትን መመዘኛዎች የሚያሟሉ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡
5. ይህ ሰው የታዘዘው ሌላ ትዕዛዝ እነዚህን የሚያመጣቸውን ሰዎች የባቢሎናውያንን ቋንቋና ሥነጽሑፍ እንዲያስተምራቸው ነው፡፡ ናቡከደነጾር እነዚህን ምርኮኞቹን ማድረግ የሚፈልገው ነገር ቢኖር አዕምሯቸውን በማጠብ ያላቸውን እምነት፣ አስተሳሰብና አመለካከት ሁሉ በአዲስ ትምህርት በመተካት ያሉበትን አለም ማለትም ባቢሎንን እንዲመስሉ ለመቅረጽ ነው ሙከራው፡፡
6. የአገር ቤት ስማቸው ዳንኤል፣ አናንያ፣ ሚሳኤልና አዛርያ ሲሆን፤ የምርኮ አገር ስማቸው ደግሞ ብልጣሶር፣ ሲድራቅ፣ ሚሳቅና አብድናጎ ነው፡፡ የነዚህን ሰዎች ስም የለወጠው ሰው የጃንደረቦቹ አለቃ አስፋኔዝ የተባለው ሰው ነበረ፡፡
7. ‹‹ብልጣሶር›› የሚለው ስም ከናቡከደነጾር አማልክት ጋራ የተያያዘ ነው፡፡ በዚህ ቅራኔ አናይም፡፡ ዳንኤል በጓደኞቹም ስም ሆኖ እንዲቀየርላቸው ሲጠይቅ የምናየው ነገር የሚሰጣቸው ምግብና የወይን ጠጅ ነው፡፡ ከዚህ መማር የምንችለው በመንፈሳዊ ህይወታችንና ለጌታ ልንኖር በምንችለው ህይወት ላይ ለውጥ ሊያመጣ በማይችል ነገር ላይ ማተኮር እንደማይኖርብንና፤ ጌታ ያዘዘንን እንዳንታዘዝ እንቅፋት በሚሆንብን ነገር ላይ ማተኮር እንደሚገባን እማራለሁ፡፡
8. እግዚአብሄር በሙሴ በኩል ምን አይነት ነገሮችን መብላት እንደሚችሉና ምን ዓይነት ነገሮችን ደግሞ መብላት እንደማይችሉ የተነገረ ስለሆነ ምናልባትም ንጉሱ ለጣዖቱ የሰዋውን ሁሉ መብላት፤ በተጨማሪም ደግሞ አሳማና የመሳሰሉት ሊቀርብላቸው ስለሚችል ከዚህ ሁሉ ለመራቅ ነው፡፡ መታዘዝ ሁኔታው በሚፈቀድበት ሥፍራ ብቻ ሳይሆን በባዕድ አገርም መታዘዝ እንዳለ እማራለሁ፡፡

# ጥናት ሶስት ዳን 1፡11-21 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. አስፋኔዝ፣ ዳንኤል፣ አናንያ፣ ሚሳኤል፣ አዛርያ፣ መጋቢውና የንጉሱን መብል የሚበሉ ወጣቶች እናያለን፡፡ በዚህ ቦታ የዳንኤል ጥያቄ ለመብል ከአትክልት ለመጠጥም ከውሃ በስተቀር ምንም ነገር እንዳይሰጣቸው ነው፡፡
2. ዳንኤል ጥያቄውን ያቀረበው በልመና መልክ ነበረ፡፡ አልስማማም፤ ምክንያቱም እምነት ስልጣንን የምንጋፋበት መሳሪያ ሳይሆን በአክብሮትና ጌታን በመታመን ተመላልሰን እርሱ የሚሰራውን ድንቅና ተአምር የምናይበት ነገር ነው፡፡ ከአቀራረቡ የምማረው በእግዚአብሄር ፊት ሞገስ ያገኘና በሰውም ፊት እግዚአብሄር ሞገስን የሰጠው ሰው በትህትና መመላለስም እንደሚቻል እማራለሁ፡፡
3. የዳንኤል አነጋገር የእምነት አነጋገር ነው ሊያሰኘን የሚችለው ነገር የአራቱን ጓደኛሞች ህይወት ብቻ ሳይሆን የጃንደረቦቹን አለቃም ህይወት ጭምር አደጋ ላይ ሊጥል የሚችል ውርርድ ነው ያደረገው፡፡ እግዚአብሄር እንዳላሳፈራቸው የምናየው በቁ15 ላይ ከሌሎቹ ወጣቶች ጤናማና ሰውነታቸው ወፍሮ መገኘቱ ያረጋግጥልናል፡፡
4. ይህንን ሰው ሃሳቡን ቀይሮ የጠየቁትን የምግብ የመጠጥ ዓይነት መስጠት እንዲቀጥል ያሳመነው ነገር በቁ16 ላይ እንደሚታየው የአራቱ ጓደኛሞች ከአስሩ ቀናት በኋላ በሰውነታቸው ላይ የታየው መልካም ለውጥ ነው፡፡ አንድ ቃል ምረጥ ብባል ‹‹ስለዚህ›› የሚለውን ቃል እመርጣለሁ፤ ምክንያቱም ስለዚህ ሲል ‹‹በዚህ ምክንያት›› ወይም ‹‹ስለሆነም›› ማለት ስለሆነ የሰውነታቸው በመልካም ሁኔታ ላይ መገኘትና የመጋቢውን ውሳኔ የሚያገናኝ ቃል ነው፡፡
5. ንጉሱ የወሰነው ጊዜ ሲባል በቁ5 ላይ እንደምናነበው የሶስት ዓመቱን ስልጠና ሲጨርሱ ማለት ነው፡፡ ንጉስ ይህንን የተገነዘበው ካነጋገራቸው በኋላ ነው፡፡ ንጉሱ ያነጋገረው አራቱን ብቻ እንዳልነበረ የሚያስገነዝበን ቃል በቁ19 ላይ የሚገኘው ‹‹ከመካከላቸው›› የሚለው ቃል ነው፡፡
6. ንጉሱ ለማወቅ የተጠቀመበት መንገድ ጥያቄን መጠየቅ ነው፡፡ የሰዎቹ ቁጥር በትክክል ባይታወቅም ‹‹በመላ ግዛቱ ካሉት አስማተኞችና ድግምተኞች ሁሉ›› ስለሚልና በዚያን ዘመን ደግሞ ባቢሎን ብዙዎቹን አገሮች የሚገዛ ስለነበረ ቁጥራቸው እጅግ ብዙ ሊሆን እንደሚችል አያጠራጥርም፡፡
7. የዚህ ዓይነት ሁኔታ ሲፈጠር ሉቃ 21፡13 እንደሚናገረው አማኝ የወንጌል መመስከሪያ ዕድል አድርጎ ሊቀበለው ይገባል፡፡ እኛ በዚህ አመለካከት ስንታጠቅ እግዚአብሄር ደግሞ ተቃዋሚዎቻችን ሊቋቋሙት እና ሊያስተባብሉት የማይችሉትን ቃልና ጥበብ እንደሚሰጠን ቃል ገብቷል፡፡
8. እነዳንኤል ሳያወላውሉ ምስክርነታቸውን በንጉሱ ፊት ሲጠብቁ እግዚአብሄር ደግሞ በራሱ በኩል ከሚያስፈልጋቸው በላይ ጥበብንና እውቀትን ሲሞላባቸው በቁ17 ላይ እንመለከታለን፡፡ መናገር ለሚፈልጉ ጊዜ ይሰጥና ተነጋገሩበት፡፡

# ጥናት አራት ዳን 2፡1-23 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ህልም አለመ፣ መንፈሱ ታወከ፣ እንቅልፍ ከእርሱ ራቀ፣ አስማተኞችን፣ ጠንቋዮችንና መተተኞችን እንዲጠሩ አዘዘ፡፡ ንጉሱ ላስጠራቸው ሰዎች የነገራቸው ሁለት ነገሮች ህልም እንዳየና፣ ከህልሙ የተነሳ መንፈሱ እንደተጨነቀ ነው፡፡
2. ኮከብ ቆጣሪዎቹ ህልሙን ለመፍታት ከንጉሱ የጠየቁት አስቀድሞ ህልሙን እንዲነግራቸው ነው የጠየቁት ሲሆን ንጉሱ ግን ከእነርሱ የሚጠብቀው ህልሙን አስቀድመው ነግረውት፤ ትርጉሙንም ጭምር እንዲያስታውቁት ነው፡፡
3. የተጠየቁትን ማድረግ ቢችሉ ስጦታ፣ ስልማት፣ ታላቅ ክብርም እንደሚቀበሉ ሲሆን የተጠየቁትን ማድረግ ባይችሉ ግን አካላቸው እንደሚቆራረጥና ቤቶቻቸውም የፍርስራሽክምር እንደሚሆን ነው፡፡ ለሁለተኛ ጊዜ የጠየቁት በቁ7 ላይ ህልሙን ለአገልጋዮቹ እንዲነግራቸው ነው፡፡
4. ንጉሱ ይህንን ጥያቄያቸውን የተረዳው ሁኔታዎች እስኪቀየሩ ድረስ ጊዜ የማራዘም ታክቲክ አድርጎ ነው፡፡ ንጉሱ ስለፍቺው የነበረው ፍርሃት የተሳሳቱ ሃሳቦችንና ክፉ ሃሳቦችን ለመንገር እንዳሰቡ ጠርጥሯቸዋል፡፡ በቁ9 መሰረት ናቡከደነጾር ህልሙ በትክክል ለመተርጎሙ እርግጠኛ ሊሆን የሚችለው አስቀድሞ ህልሙ ሲነገረውና ከዚያም የህልሙ ትርጓሜ ምን እንደሆነ ሲነገረው ነው፡፡
5. ጥያቄውን ሊመልስ የሚችል ሰው በምድር ላይ እንደሌለ፣ እንደዚህ አይነት ጥያቄ በማንም ተጠይቆ አያውቅም፣ ጥያቄው እጅግ አስቸጋሪ ነው፣ በሰው መሃል የማይኖሩ አማልክት መግለጽ እንደሚችሉ፡፡ በሃሳባቸው እስማማለሁ፤ ምክንያቱም በሰው ልብ ውስጥ ያለውንና በአዕምሮ ውስጥ የሚከናወነውን ሊናገር የሚችል ሳይሆን አምላክ መሆን አለበት፡፡
6. በኮከብ ቆጣሪዎቹ መልስ የተናደደው ንጉስ በባቢሎን የሚኖሩ ጠቢባን ሁሉ እንዲገደሉ አወጀ፡፡ ዳንኤል ያደረገው ነገር አርዮክን ማነጋገር፤ ስለንጉሱ አዋጅ ጥያቄ መጠየቅና፣ ህልሙን ለመተርጎም ጊዜ እንዲሰጠው መጠየቅ ነበረ፡፡ የዘበኞቹን አለቃ አርዮክን ሲያነጋግር በጥበብና በዘዴ መሆኑ እኛም ዘዴንና ጥበብን መጠቀም እንደሚያስፈልገን ሲያስተምረን፣ ሌላው ልንማር የምንችለው ደግሞ ነገር ደግሞ፤ ጊዜ እንዲሰጠው እንደጠየቀ እኛም ውሳኔ በሚያስፈልጋቸው ነገሮች ላይ ጊዜ መውሰድና ረጋ ማለትን ያስተምረናል፡፡
7. ዳንኤል በቤቱ ተመልሶ ያደረገው ነገር ለሶስቱ ጓደኞቹ ሁኔታውን መንገርና በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ ስለ ሁኔታው ወደ አምላካቸው እንዲጸልዩ ነገረ፡፡ ይህ የሚያስተምረኝ የመጀመሪያውን ብቻ አድርጎ ቢተው እንደማንኛውም አልባሌ ወሬ ሆኖ ሊቀር ይችል ነበረ፤ ነገር ግን በጸሎት መቅረባቸው ለብዙዎች ህይወት የሚሆን መልስ አመጣ፡፡ ስለዚህ እኛም በወሬ የምናቆማቸው ብዙ ጸሎት የሚያስፈልጋቸው ነገሮች አሉና በወሬ ጀምረን በወሬ እንዳንጨርስ እንድናስተውል ያስተምረናል፡፡
8. ጊዜንና ወቅትን ይለውጣል፣ ነገስታትን በዙፋን ያስቀምጣል፣ ነገስታትን ያዋርዳል፣ እውቀትን ለሚያስተውሉ ይሰጣል፣ የጠለቀውንና የተሰወረውን ይገልጣል፣ በጨለማ ያለውን ያውቃል፣ ብርሃን ከእርሱ ጋራ ይኖራል፡፡
9. እግዚአብሄር ስጦታን ሲሰጥ የተሰጠንን ተቀብለን ከእርሱ ጋራ ግንኙነት በሌለው መንገድ እንደራሳችን እቃ በፈለግነው ሰዓት እየመዘዝን የምንጠቀምበት እንዳልሆነ፤ ነገር ግን ከእግዚአብሄር ጋራ በመወያየት ሌሎችን የምናገለግልበት መሳርያ እንደሆነ እማራለሁ፡፡

# ጥናት አምስት ዳን 2፡24-49 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ዳንኤል ያደረገው ነገር ወደ አርዮክ ተመልሶ በመሄድ የባቢሎን ጠቢባን እንዳይገደሉና ህልሙን ለመተርጎም ወደ ንጉሱ እንዲወስደው ጠየቀው፡፡ አርዮክ ‹‹አግኝቻለሁ›› የሚለው ፈልጎ እንዳገኘ እንጂ ዳንኤል ወደ እርሱ እንደመጣ ስለማይጠቁም፤ ምናልባት ለሹመትና በንጉሥ ፊት ተቀባይነት ለማግኘት የተጠቀመበት አነጋገር ይሆናል ብዬ እገምታለሁ፡፡
2. ሌሎቹ ጠቢባን በዳን 2፡10 ላይ እንደተናገሩት ህልሙን መፍታት የሚችል ከሰዎች መሃል እንደሌለ ዳንኤልም ይስማማል፡፡ ልዩነታቸው ኮከብ ቆጣሪዎቹ ህልሙ ሊፈታ የሚችለው በአማልክት እንደሆነ ሲናገሩ ቁ12፤ ዳንኤል ግን አንዱ አምላክ በሰማይ ያለው ብቻ ምሥጢርን ይገልጣል ይለናል ቁ28፡፡
3. ምስጢሩን የገለጠበት ምክንያት ንጉሱ የህልሙን ትርጉሙ እንዲያውቅና እንዲረዳ ነው፡፡ እኔ የማየው ግሩም ባህርይ ትህትና ነው፤ ይህንንም ያልኩት እግዚአብሄር በብዙ ጥበብ የባረከው ሰው እንደሆነ በብዙ የተነገረለት ሆኖ እያለ በቁ30 ላይ የተናገረው አነጋገሩ ትልቅ ትህትና ያለበት እንደሆነ ያሳያል፡፡
4. ንጉሱ ያየው ምስል ራሱ ንጹህ ወርቅ፣ ደረቱና ክንዶቹ ብር፣ ሆዱና ጭኖቹ ናስ፣ እግሮቹ ከፊሉ ብረት ከፊሉም ሸክላ ነበረ፡፡ ይህንን እያየ እያለ አንድ ድንጋይ ወርዶ የምስሉን እግሮች መትቶ አደቀቃቸው፡፡ ምስሉ ተሰባብሮ እንደ እብቅ ሆነ ነፋስም ጠራርጎ ወሰደው፡፡
5. ምስሉን ያደቀቀው ድንጋይ ከየት እንደመጣ አልነገረንም፤ ነገር ግን የሰው እጅ እንዳልነካው ግልጽ ያደርግልናል፡፡ የዚህን ድንጋይ መጨረሻ ዳንኤል በቁ35 ላይ ሲናገር ታላቅ ተራራ እንደሆነና ምድርን እንደሞላ ይናገራል፡፡
6. እዚህ ላይ ሶስቱን ጓደኞቹንም በጸሎት አንድነት ሁሉ ስለተካፈሉ እነርሱም የዚህ በረከት ተካፋዮች እንደሆኑ ሲጠቁም ነው፡፡ ከዚህ አድራጎቱ የምማረው በእኔነት ሳንጠመድ እግዚአብሄር የሰጠን ስጦታ የሁላችን በረከት እንደሆነ ማየት መቻል ጥበብ መሆኑን ነው፡፡ ዳንኤል ለነገስታት ዙፋን እንደሚሰጥ፤ ሲፈልግም ደግሞ እንደሚያዋርድ ሲናገር ይህም ክፍል ይህንን ሃሳብ የሚያጠናክር ነው፡፡
7. ናቡከደነጾር በቁ38 እንደሚታየው በወርቅ ተመስሏል፡፡ ከብር የተሰራው ቁ39 የሚነግረን በአጭሩ ከናቡከደነጾር ያነሰ ሲሆን፤ ከናስ የተሰራው ደግሞ በ39 መላውን ምድር እንደሚገዛ እናነባለን፡፡ ይህ አራተኛው መንግስት ከእርሱ በፊት የነበሩትን ሁሉ ያደቃቸዋል፣ የተከፋፈለ መንግስት ይሆናል፣ ከፊል ብርቱ ከፊል ደካማ ይሆናል፤ ህዝቡ በአንድነት አይኖሩም፡፡
8. የህልሙ መፈታት ያስገኛቸው ሁለት ግልጽ የሆኑት ውጤቶች፤ የእግዚአብሄር ስም ከስሞች በላይ መሆኑ ተረጋገጠ (ቁ47)፤ ሌላው ደግሞ የእግዚአብሄር ባሪያዎች የክብር ቦታ መሰጠቱ ቁ48-49) ሲሆን ሌሎች ሁለት ግልጽ ያልሆኑት ደግሞ ሌሎቹ የባቢሎን ጠቢባን ከሞት መትረፍና (ቁ12)፣ የንጉሱ ናቡከደነጾር ከመንፈስ ጭንቀት መዳን ናቸው፡፡ (ቁ3)
9. እርሱ የሚመሰርተው መንግስት ፈጽሞ የማይፈርስ፣ ለሌላ ህዝብ የማይሰጥ፣ መንግስታትን ሁሉ የሚያደቅና የሚያጠፋ፣ ለዘለዓለም ደግሞ ጸንቶ የሚኖር መንግስት ነው፡፡ መንግስቱ የሚመሰረተው በእነዚህ መንግስታት ዘመን እንደሆነም እንረዳለን፤ ማለትም መንግስቱ በግልጽ ባይታይም በሁሉም ዘመን ውስጥ እንዳለና ነገር ግን በመጨረሻ ሁሉን አጥፍቶ ለዘላለም የሚኖረውን ይመሰርታል፡፡

# ጥናት ስድስት ዳን 3፡1-18 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. የምስሉ መጠን ከፍታው ስልሳ ክንድ፣ ወርዱ ደግሞ ስድስት ክንድ ነበረ፡፡ ለምስሉ ምርቃት የተጠሩት መኳንንት፣ ሹማምንት፣ አገረ ገዢዎች፣ ዳኞች፣ የህግ አዋቂዎችና በየአውራጃው ያሉ ሹማምንት ሁሉ ናቸው፡፡
2. እነዚህ ሶስት ጓደኞሞች ወደ ምርቃቱ ሊጠሩ የቻሉት በ2፡49 ላይ እንደምናየው በዳንኤል አሳሳቢነት ንጉሱ የባቢሎን አውራጃ አስተዳዳሪዎች ሆነው ስለተሾሙ ነው፡፡ በዚህ ቦታ የታወጀው የተለያዩ የሙዚቃ መሳሪያዎች ድምጽ ሲሰማ ሹማምንቱ ሁሉ ናቡከደነጾር ላቆመው ምስል እንዲሰግዱ የሚናገር ነበረ፡፡ ከእነሲድራቅ ድርጊት የምማረው በአንድ በኩል የበላይን መታዘዝና፣ በሌላ በኩል ደግሞ ቃሉ የማይፈቅድልንን ነገር የንጉስ ትዕዛዝ እንኳን ቢሆን እንቢ ለማለት መቁረጥን ነው፡፡
3. ሹማምንቱ መጀመሪያ ሲጠሩ ለስግደት አልተጠሩም፤ የተጠሩት ንጉሱ ያቆመውን የወርቅ ምስል ለመመረቅ ነበረ፡፡ በእኔ አመለካከት ሹማምንቶቹን ለምስሉ እንዲሰግዱ ማድረግ አስቀድሞ ያሰበውና ነገር ግን ሰዎቹ ሳይዘጋጁ እንደ ዱብዳ ያወረደባቸው ይመስለኛል፡፡ እያንዳንዱ ለራሱ ይመልስ፡፡
4. ባልሰገደ ሰው የሚወሰደው እርምጃ ወዲያውን በሚንበለበለው የእሳት እቶን ውስጥ መጣል ነው፡፡ የንጉስ አዋጅ ሙሉ ለሙሉ ተፈጻሚነት አግኝቷል ማለት የምንችለው ስገዱ የተባት ሁሉ ሰግደዋል፤ ያልሰገዱ ይደርስባቸዋል የተባው ማስፈራሪያም ሥራ ላይ ውሏል፡፡ ለምስሉ የሰገዱትን ሲጠቅስ፤ ህዝብ ሁሉ፣ መንግሥታት፣ ልዩ ልዩ ቋንቋ የሚናገሩ ሰዎች በማለት ይዘረዝራቸዋል፡፡
5. ሶስቱ ጓደኞሞች የተከሰሱባቸው ሶስቱ ክሶች፡ ትዕዛዝህን አይቀበሉም፣ አማልክትን አያገለግሉም፣ አንተ ላቆምከው የወርቅ ምስል አይሰግዱም የሚሉት ናቸው፡፡ ክሱን ያቀረቡት ቁ8 እንደሚናገር አንዳንድ ኮከብ ቆጣሪዎች ናቸው፡፡ ከክሶቹ ሁለቱ በማያጠራጥር መንገድ ለትክክል ሲሆኑ፤ ትዕዛዝህን አይቀበሉም የሚለው ስለየትኛው ትዕዛዝ እንደሚናገር ማጤንና ከዚያ አንጻር የሚመለስ ይሆናል፤ ምክንያቱም ለንጉስ መታዘዝ አንደኛው የእግዚአብሄር ትዕዛዝ ስለሆነ ማለት ነው፡፡
6. ‹‹ትዕዛዝህን አይቀበሉም›› የሚለውን ከእርሱ ጥያቄ ውስጥ አላስገባውም፡፡ በምዕ 2፡47 ላይ የእነርሱ አምላክ የአማልክት ሁሉ አምላክና፤ የነገስታትም ጌታ እንደሆነ ተናግሮ በዚህ ክፍል ግን ከእጁ ሊያድናቸው የሚችል እንደሌለ መናገሩ ቀድሞውንም በመረዳት የተናገረው ነገር እንዳልሆነና ራሱን በራሱ እየተቃረነ እንደሆነ ማየት ይቻላል፡፡
7. በጭራሽ አልስማማም! ምክንያቱም እነዚህ ሰዎች አስቀድመው አምላካቸው ሊያድንናቸው ችሎታ እንዳለው፤ በቁ15 ላይ ላቀረበው ጥያቄ መልስም ‹‹ከእጅህም ያድነናል›› በማለት እንዳረጋገጡለት ስናይ፤ ‹‹ባያድነንም እንኳ›› የሚለው አነጋገር የውሳኔያቸውን ቆራጥነት ለማሳየት እንጂ ጥርጥር እንደነበራቸው አያሳይም፡፡ ዕብ 11፡33-34ትም የሚያሳየን ‹‹እነዚህ በእምነት…የእሳትን ሃይል አጠፉ›› በማለት የእምነት ጀግኖች እንደሆኑ ያረጋግጥልናል፡፡ ‹‹ባያድነንም እንኳ›› የሚለው አነጋገር ለብዙዎች እምነት የጎደለው ሰው አባባል ነው፤ ነገር ግን ከነዚህ ጀግኖች ያ አለመሆኑን እንማራለን፡፡
8. እነዳንኤል በእነዚህ ቁጥሮች ሲያደርጉ የሚታየው የባቢሎንን ጠቢባን ከሞት እንዲድኑ ለእግዚአብሄር ጸሎትና ለንጉሱ ደግሞ ጥያቄ ሲያቀርቡ ነው፡፡ የባቢሎን ጠቢባን ደግሞ በተቃራኒው ሶስቱን ጓደኞሞች እንዲገደሉ ወጥመድ ሲያበጁ እናያለን፡፡ ሌላውን እያንዳንዱ የግል መልሱን ይስጥበት፡፡

# ጥናት ሰባት 3፡19-30 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ንጉሱ በሶስቱ ጓደኛሞች እጅግ እንደተቆጣ፣ በእነርሱ ላይ ፊቱ እንደተለወጠባቸው፣ የእሳቱ ሃይል እንዲጨመር ማዘዙ፣ ከሰራዊቱ ብርቱ ወታደሮችን መምረጡ የነበረውን ብስጭት ያሳየናል፡፡ ስሜት አይሰጥም ብዬ የማስባቸው ሁለት ሲሆኑ፤ የመጀመሪያው እሳቱን ከልክ በላይ እንዲነድ ማድረጉ ሰዎቹ በቶሎ እንዲሞቱ ያደርጋል፤ ነገር ግን ቀስ ብሎ መንደዱ ስቃያቸውን ያራዝማል እላለሁ፤ በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ ሲድራቅና ሚሳቅ እንቢ አንገባም ብለው የሚታገሉ ሰዎች ወይም መሳሪያ ይዘው ራሳቸውን የሚከላከሉ ስላልሆኑ ብርቱ ወታደሮችን መምረጥ ስሜት አይሰጥም እላለሁ፡፡
2. ቁ20, 21, 23 ተጠፍረው ታስረው ነበረ፣ ቁ21 ሁሉ ነገራቸውን እንደለበሱ ነበረ እሳቱ ውስጥ የገቡት፣ አስገብቶ ማቆም ሳይሆን እንዲወረወሩ ወይም እንዲጣሉ ነው የተደረገው፡፡ የእሳቱን ሃይለኛነት ሊያረጋግጥልን የሚችለው ቁ22 ላይ ያለው ‹‹…የጣሏቸውን ወታደሮች ገደላቸው፤፤›› የሚለው አነጋገር ነው፡፡
3. ንጉሱን ያስደነቀው ነገር በመጀመሪያ ደረጃ ሰዎቹ ሲጣሉ ታስረው ነበረ አሁን ግን የሚያያቸው ያልታሰሩ ሰዎች ናቸው፤ ሁለተኛ ደግሞ የተጣሉት ሰዎች ቁጥር ሶስት ሲሆን አሁን የሚያየው ግን አራት ሰዎች ነው፤ ሌላው አስደናቂ ነገር ደግሞ አራተኛ ሆኖ የሚታየው እንደማንኛውም ሰው ሳይሆን የአማልክትን ልጅ ይመስላል፤ እነዚህ ሁሉ ናቸው ያስደነቁት እላለሁ፡፡ እግዚአብሄር አንዱን በመከራ ውስጥ በተአምር ማውጣት እንደሚችልና፣ በሌላ በኩል ደግሞ በመከራ ውስጥ ህይወታቸውን ለርሱ ክብር እንዲሰው የሚፈቅድበት ወቅቶችም ሊኖር እንደሚችል እማራለሁ፡፡
4. በዚህ ስፍራ ጓደኛሞቹን የጠራቸው ‹‹የልዑል አምላክ አገልጋዮች›› በማለት ነበረ፡፡ በቁ26 እና በቁ19 ሲታይ ንጉሱ በ19 ላይ በቁጣና በንዴት መንፈስ ውስጥ እንደነበረ ስናነብ፤ በቁ26 ደግሞ በተረጋጋ፣ በትህትና መንፈስ ውስጥ እንደነበረ እንመለከታለን፡፡
5. ምስክር ሊሆኑ የሚችሉት፡ ንጉሱ፣ መኳንንቱ፣ ሹማምንቱ፣ አገረገዢዎቹ፣ የቤተመንግስት አማካሪዎቹ ሁሉ ነበሩ፡፡ ሰዎቹ ሊመሰክሩ የሚችሉት፡ እሳቱ ሰውነታቸውን እንዳልነካ፣ ከራሳቸው ጠጉር አንዲቱ እንኳን እንዳልተቃጠለች፣ የመጎናጸፊያቸው መልክ እንዳልተለወጠና የእሳት ሽታም በላያቸው ላይ እንዳልነበረ ሊመሰክሩ ይችላሉ፡፡
6. ድፍረት የሆናቸው ነገር ቁ28 ‹‹በእርሱ በመታመን›› እንደሆነ ይነግረናል፡፡ ህይወታቸውን እስከመስጠት ድረስ ያደረሳቸው ነገር፤ ከአምላካቸው በቀር ሌላ አምላክ ለማገልገልም ሆነ ለሌላ ለመስገድ ፈቃደኛ ባለመሆናቸው ነው፡፡
7. ንጉሱ በግሉ የደረሰበት ውሳኔ እንደዚህ የሚያድን ሌላ አምላክ (የእርሱንም አምላክ ጨምሮ) እንደሌለ ሲሆን፤ በእነ ሲድራቅ አምላክ ላይ ምንም ዓይነት ክፉ ሊነገር እንደማይችል አዋጅ ማወጅ ነበረ፡፡ እነዚህ ጓደኛሞች ታሪኩ ሲፈጸም በሹመት እንደተጨረሰ ቁ30 ይነግረናል፡፡
8. እነዚህ ሶስት ሰዎች እንኳን ሹማምንቱን ሁሉ ቀርቶ ጥቂቶቹን ለማግኘት ትልቅ ሥራ እንደሚሆን ሲታወቅ በዚህ ጊዜ የተገኙትን ሁሉ ለማግኘት የማይሞከር ነገር ነው፡፡ እግዚአብሄር ለልጆቹ መጥፊያ ሰይጣን ያዘጋጀውን ክፉ ሁኔታ ተጠቅሞ በምንም መንገድ በአንድነት ሆነው የአምላካችንን ክብር መመስከር የማይችሉትን ሰዎች ክብሩን ማየት እንዲችሉ በማድረግ ሁኔታውን ገልብጦ አይተናል፡፡

# ጥናት ስምንት ዳን 4፡1-18 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ንጉሱ ሃሳቡን ማስተላለፍ የፈለገው በቁ1 ላይ እንደተጻፈው በምድር ሁሉ ለሚኖሩ ህዝቦች፣ ለመንግሥታትና፣ ልዩ ልዩ ቋንቋዎችን ለሚናገሩ ሰዎች ሁሉ ነበረ፡፡ እነዚህ ቁጥሮች እንደሚነግሩን ዋነኛ ሃሳቡ የመልዕክቱ፤ ልዑል እግዚአብሄር ያደረገለትን ነገር ለመናገር ነው ይላል፡፡
2. መልዕክቱን ሲያስተላልፍ እጅግ ደስ በተሰኘ ልብ እንደሆነ እንደሆነ ከራሱ አፍ ይሰማል፡፡ የምልክቱ ታላቅነት፣ የድንቁን ብርቱነት፣ የመንግሥቱን ዘላለማዊነትና፣ የግዛቱ ከትውልድ እስከ ትውልድ መኖር ናቸው፡፡
3. ኑሮው በቤተ መንግሥት እንደሆነ፣ ደልቶት የሚኖር እንደሆነ፣ ምቾት የሞላው ኑሮ እንደነበረው ማየት ይቻላል፡፡ በዚህ ሁኔታ እያለ አንድ የሚያስፈራ ህልም ተመለከተ፤ ይህ ሁኔታም በህይወቱ የፈጠረው ነገር ፍርሃትና ድንጋጤን ለቀቀበት፡፡ ከዚህ የምማረው ሰው ምንም ያህል ቢሳካለትና ሁሉ ነገር ቢሞላው እነዚህ ነገሮች ሰላምና እረፍትን ሊሰጡት እንደማይችሉ ነው፡፡
4. በ2፡1-6 ያለው ላይ ጠቢባኑም ሆኑ ዳንኤል የተጠየቁት የህልሙን ፍቺ እንዲነግሩ ብቻ ሳይሆን፤ ህልሙንም ራሳቸው ተናግረው እንዲፈቱ ነበረ፤ ነገር ግን በዚህ ክፍል በ4፡7 እና 8 እንደምናየው ህልሙ ተነግሯቸው የሚጠበቅባቸው ትርጉም ብቻ ስለሆነ ከዚያኛው ቀለል ይላል፡፡
5. ንጉሱ ያየው ነገር እጅግ ረጅም ዛፍ ነው፡፡ ዛፉ እጅግ አደገ፣ ጠነከረ፣ ጫፉ ሰማይ ደረሰ፣ ቅጠሎቹ ያማሩ፣ ፍሬዎቹ የተንዠረገጉ ነበሩ፣ ለሁሉም የሚሆን ምግብ ነበረበት…ይቀጥላል፡፡
6. መልዕክቱን ያስተላለፈው በቁ13 ላይ የምናየው ‹‹ቅዱስ መልዕክተኛ›› በማለት የተጠቀሰው፤ ምናልባትም የእግዚአብሄር መልአክ እንደሚሆን ይገመታል፡፡ የመልዕክቱ አጠቃላይ ሃሳብ፤ ይህ ከላይ የተመለከትነው ዛፍ እንዲቆረጥ፣ እንዲጨፈጨፍ፣ ቅጠሉ እንዲራገፍ፣ ፍሬው እንዲበተን፤ ጉቶው ግን በብረትና በናስ ታስሮ በመሬት ውስጥ ውስጥ እንዲቆይ፣ በሰማይ ጠል እንዲረሰርስ፣ ለሰባት ዓመታትም በጥሻ ውስጥ ከአራዊት ጋራ እንዲኖር የሚል ነበረ፡፡
7. ይህ ሁሉ በዛፉ ላይ የሚመጣው፤ ልዑል በሰዎች መንግሥታት ሁሉ እንደሚገዛና እነዚህንም መንግስታት ለወደደው እንደሚሰጥ፣ ከሰዎችም የተናቁትን በላያቸው እንደሚሾም ህያዋን ሁሉ ያውቁ ዘንድ ነው፡፡ የተቀረውን ጥያቄ እያንዳንዱ በየግሉ ይመልስ፡፡
8. ንጉሱ ለጥያቄው መልስ አስቀድሞ የፈለገው ከባቢሎን ጠቢባን ሲሆን በመጨረሻ ግን ሁሉ ሲደፋፈንበትና ጭልም ሲልበት ለመፍትሄ ወደ እግዚአብሄር ሰው ዘወር እንዳለ እናነባለን፡፡

# ጥናት ዘጠኝ ዳን 4፡19-37 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ዳንኤል በዚህ ቦታ የተሰማው ስሜት ለጥቂት ጊዜ በጣም እንደታወከና ሃሳቡም እንዳስደነገጠው እንመለከታለን፡፡ ይህ ዓይነቱ ስሜት ሊሰማው የቻለው በእኔ አመለካከት ንጉሱን የሚወደውና የሚያከብረው ስለሆነ ይመስለኛል፤ ይህንንም ማለት የቻልኩት ቁ19 ላይ ‹‹ህልሙ ለሚየሉህ ይሁን፣ ትርጉሙም ለጠላቶችህ›› ከሚለው አነጋገር ነው፡፡
2. ናቡከደነጾር በቁ22 ላይ እንደምናየው የተመሰለው በዛፍ ነበረ፡፡ ያደገና የጠነከረ ነው፣ ጫፉ ከሰማይ የደረሰና በምድር ሁሉ የሚታይ ነው፣ ቅጠሎቹ ያማሩና ፍሬውም ለሁሉ ምግብ የሆነ ነው፣ የዱር አራዊት መጠለያ ነው፣ ቅርንጫፎቹ ለሰማይ ወፎች ጎጆ መስሪያ ነበረው፡፡ መልዕክተኛው የተናገረው ደግሞ ዛፉን ቁረጡ፣ አጥፉት፣ ታስሮ በመሬት ውስጥ ይቆይ፣ በሰማይ ጠል ይረስርስ፣ እንደ ዱር አራዊት ይኑር፣ ሰባት ዓመትም ይለፍበት የሚል ነበረ፡፡
3. አዋጁን ያወጣው እግዚአብሄር ራሱ ነው፡፡ በነገስታት ንጉስ ላይ አዋጅ ማወጅ መቻሉ ከእግዚአብሄር ሥልጣን በላይ የሆነ ማንም እንደሌለና የወደደውን ማድረግም እንደሚችል ያሳየኛል፡፡
4. የዛፉ ጉቶ ከስሩ ተነቅሎ እንዳይጣልና ነገር ግን በብረትና በናስ ታስሮ በመሬት ውስጥ እንዲቆይ መደረጉ ንጉሱ በንስሃ እንዲመለስ እግዚአብሄር ጊዜ እንደሰጠውና እንደሚጠብቀው፤ በትህትና ስልጣን ሁሉ ከሰማይ መሆኑን ሲያውቅ ደግሞ ሊመልስለት እንዳሰበ ያስረዳናል፡፡ አራቱ የዳንኤል ምክሮች ሃጥያት መስራትን እንዲተው፣ ትክክለኛ የሆነውን እንዲያደርግ፣ ክፋትን እንዲተውና ለተጨነቁት ቸርነትን እንዲያደርግ የሚሉት ናቸው፡፡
5. የመጀመሪያው ልዑል በሰዎች መንግስት ሁሉ ላይ ሙሉ ስልጣን እንዳለውና፤ ሁለተኛው ደግሞ መንግስታትን ሁሉ ለወደደው መስጠት እንደሚችል የሚሉት ናቸው፡፡ በቁ28-30 ያለው ደግሞ የንጉሱን ትዕቢትና ሁሉ ነገር በራሱ ቁጥጥር ስር እንደሆነ የሚናገረው የትዕቢት ንግግር ነው፡፡
6. አንድም ሳይቀር የተነገረው ሁሉ ነው የተፈጸመበት፡፡ ይህ ክፍል በማር 13፡31 ለተጻፈው ክፍል በተግባር ሥራ ላይ ሲውል በግልጽ የሚያሳይ ሲሆን ቃሉ በትናንሾች ላይ ብቻ ሳይሆን በነገሥታት ሁሉ ላይ በስልጣን የሚሰራ እንደሆነም ማየት ይቻላል፡፡
7. በቁ28-30 የምንመለከተው ትዕቢተኛና ማን አለብኝ የሚል ሰው ሲሆን፣ በቁ34-35 ግን ራሱን ከአምላክ በታች ያስገዛና አምላክን የሚያመሰግን ሰው እንመለከታለን፡፡ 1ኛ ጴጥ 5፡5 ‹‹እግዚአብሄር ትዕቢተኞችን ይቃወማል፤ ለትሁታን ጸጋን ይሰጣል›› የሚለውን ክፍል ያስታውሰኛል፡፡
8. የውርደቱ ጊዜ ሲፈጸም ንጉሱ በመጀመሪያ የወሰደው እርምጃ ዓይኖቹን ወደ ሰማይ ማንሳት፣ ልዑልንም መባረክ፣ መወደስና ክብርን መስጠት ነበረ፡፡ ንጉሱን ለምስጋና ያነሳሱት ስለ እግዚአብሄር ባህርይ የተማራቸው ሁለት ነገሮች የመጀመሪያው አምላክ የሚያደርገው ሁሉ ትክክል መሆኑና ሌላው ደግሞ መንገዶቹ ሁሉ ጽድቅ እንደሆኑ ነው፡፡

# ጥናት አስር ዳን 5፡1-17 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. በተደጋጋሚ የተጠቀሰው አንድ ቃል መጠጣት የሚለው ስሆን፤ የዚህ ቃል መደጋገም በዚህ ስፍራ ስለነበረው መንፈስ የሚነግረን የስካርና ከቁጥጥር ውጭ የሆነ ሁኔታ ሊኖር እንደሚችል እረዳለሁ።
2. የሚጠጣባቸው እቃዎች የህያው እግዚአብሄር ንብረቶች ሲሆኑ፤ ሰዎቹ እየጠጡ የሚያመሰግኑት ግን ቁ4 እንደሚነግረን የወርቅና የብር፣ የናስና የብረት፣ የእንጨትና የድንጋይ አማልክትን ነበረ። በንጉስ ቤተመንግስት መጠጫ ጠፍቶ ሳይሆን፤ የትዕቢቱ ብዛት ሲገለጥና ዳንኤል ንጉሱ ያየውን ነገር ትርጉም በተናገረበት ጊዜ ከተናገራቸው ነገሮች በመነሳት ይህ ሰው በህያው እግዚአብሄር ላይ ያለውን ተግዳሮት ለማሳየት ፈልጎ ሊሆን እንደሚችል እገምታለሁ።
3. በንጉሱ ላይ የተከሰቱት ስሜቶች፡ በድንጋጤ ተሞላ፣ ፊቱ ተለዋወጠ፣ እግሮቹና እጆቹ ከዱት፣ ጉልበቶቹ ተብረከረኩ። ንጉሱ ወዲያው የወሰደው እርምጃ አስማተኞችን፣ ኮከብ ቆጣሪዎችንና መተተኞችን ማስጠራት ነበረ። ጽህፈቱን አንብቦ ለተረጎመለት ሰው ሃምራዊ መጎናጸፊያ ማልበስ፣ የወርቅ ሃብል በአንገቱ ላይ ማጥለቅና፣ በመንግስቱ ላይ ሶስተኛ ገዢ ማድነግ ነበረ።
4. ጽሁፉን አንብቦ የሚተረጉም ባለመገኘቱ የንጉሱ ፍርሃት የበለጠ እየጨመረ እንደመጣና ፊቱም ከበፊቱ የበለጠ እንደተለወጠ ሲታይ፤ እርሱ ብቻ ሳይሆን መኳንንቱም ሁሉ ግራ ተጋብተው ሲደናገጡ ይታያል። በዚህ ክፍል የንግስቲቱ ምክር ለንጉሱ በተለይ በቁ12 ላይ እንደምናየው ዳንኤል የተባለው ሰው ጽሁፉን ሊያነብልህና ትርጉሙን ሊነግርህ ስለሚችል እርሱን አስጠራ የሚል ነበረ።
5. ስለዳንኤል ሰምቻለሁ የሚላቸው ነገሮች የአማልክት መንፈስ በውስጡ እንዳለ፣ እውቀት፣ ማስተዋልና ልዩ ጥበብ እንዳለው፣ አስቸጋሪ የሆነውን ነገር መፍታት እንደሚችል ነው። ንግስቲቱ ዳንኤል ‹‹የቅዱሳን አማልክት መንፈስ›› እንዳለበት የምትናገር ሲሆን፤ ቤልሻዛር ደግሞ የሚናገረው ‹‹የአማልክት መንፈስ›› በውስጡ እንዳለ ነው፤ ንግስቲቱ ትክክለኛውን ብላለች ማለትም ዳንኤል የቅዱሱ የእግዚአብሄር መንፈስ የነበረበት ሰው ነው።
6. ይህ አነጋገር ዳንኤልን ከሌሎቹ ጠቢባንና አስማተኞች ለመለየት የተነገረ አነጋገር ነው። ዳንኤል ጽሁፉን አንብቦ ቢተረጉም በቁ7 ላይ ልክ ለሌሎቹ አስማተኞችና ጠቢባን እንደተነገረው ሃምራዊ መጎናጸፊያ፣ የወርቅ ሃብልና የመንግስት ሶስተኛ ገዢ መሆን ቃል ተገብቶለታል።
7. የዳንኤል ምላሽ ‹‹ስጦታዎችህን ለራስህ አድርግ፤ ሽልማቶችህንም ለሌላ ሰው ስጥ›› የሚል ነበረ። በእኔ አመለካከት ለሁለቱ ነገስታት ያሳየውአቀራረብ የተለያየ ሆኖ ይታየኛል፤ ይህንንም ማለት ያስቻለኝ በ4፡19 ላይ ሁኔታው እንደረበሸውና ለንጉሱም ደግሞ ሊመጣበት ያለውን ነገር ለጠላቶቹ ቢሆን እንደሚመርጥ ሲናገር፤ ለቤልሻዛር ግን የዚያን አይነት መቆርቆር አላሳየም፤ ለዚህም የሚመስለኝ የአምላኩን ቤት እቃ ለእርሱ መጠጫነት በድፍረት አምጥቶ ስለጠጣበት ሊሆን እንደሚችል እገምታለሁ።
8. መልካም መንፈስ፣ እውቀትና ማስተዋል፣ ህልምን መተርጎም፣ እንቆቅልሽን መፍታት፣ የተሰወረውን የመግለጥ ልዩ ችሎታ ነበረው። ከዝርዝሮቹ በአንደኛነት የተቀመጠው ‹‹መልካም መንፈስ›› እንደነበረው የሚገልጸው ነው።

# <u>ጥናት አስራ አንድ ዳን 5፡18-31 (ለመሪው የተዘጋጀ)</u>

1. ከልዑል አምላክ የተሰጠው ገናናነት፣ ታላቅነት፣ ክብር፣ ግርማና ሥልጣን ነው፡፡ ሰዎችም ሁሉ ለእርሱ የተንቀጠቀጡለት ምክንያት እግዚአብሄር ከሰጠው ታላቅ ሥልጣን የተነሳ ነበረ፡፡
2. ይህ ‹‹የፈለገውን›› የሚለው ቃል ነው አራት ጊዜ ተጠቅሶ የሚታየው፡፡ በናቡከደነጾር ልብ ውስጥ ይህ የፈለገውን የማድረግ ሥልጣን ያመጣው ትዕቢትንና እግሪትን ነው፡፡
3. ይህ ንጉስ የደረሰበት ሁኔታ፡ ከዙፋን መውረድ፣ የክብር መገፈፍ፣ ከሰው መካከል መሰደድና የመሳሰሉትን ሁሉ ይጨምራል፡፡ ንጉሱ በዚህ በተዋረደ ሁኔታ እንዲቆይ የተደረገበት ጊዜ፤ ልዑል አምላክ በሰዎች መንግሥት ላይ እንደሚገዛና እነርሱንም ለወደደው እንደሚሰጥ እስከሚያውቅበት ጊዜ ድረስ ነው፡፡
4. ‹‹ለንጉስ ቤልሻዛር የታሪክ ማስታወሻ›› ‹‹የዳንኤል ስብከት ለንጉሱ›› ማለት እንችላለን፡፡
5. ማየት፣ መስማትና ማስተዋል የማይችሉ ብሎ ነው ዳንኤል የሚናገርላቸው፡፡ ንጉሱ ሌላ ያጠፋው ትልቅ ጥፋት ህይወቱንና መንገዱን በእጁ የያዘውን አምላክ አለማክበሩ እንደሆነ ዳንኤል አረጋግጦ ይነግረዋል፡፡
6. ዳንኤል ሃምራዊ መጎናጸፊያ፣ የወርቅ ሃብልና ሶስተኛ ገዢ የመሆን ስጦታ ነው የተሰጠው፡፡ በቁ17 ላይ እንደምናነበው ዳንኤል የስጦታው ፍላጎት እንዳልነበረው ግልጽ አድርጎ ለንጉሱ ፊት ለፊት እንደነገተው ተመልክተናል፤ ስለዚህ ለስጦታ ተረገመ የሚለው ሃሳብ ስሜት አይሰጥም፡፡
7. የናቡከደነጾር ሰፋ ያለጊዜ እንደተሰጠው ስንመለከት፤ ቤልሻዛር ግን ወዲያው ፍርዱ መጣበት፤ የንስሃ እድል ለናቡከደነጾር የተሰጠ ሲሆን ለቤልሻዛር ግን አልተሰጠም፡፡
8. የዚህ ሰው በደል ከብዶ የተገኘው በቁ22 ላይ ‹‹አንተ ልጁ ሆነህ ይህንን ሁሉ ብታውቅም›› የሚለው አነጋገር በአባቱ ላይ ሲደርስ ያየው ፍርድ እርሱ ራሱን በትህትና እንዲኖር ሊያደርገው ይገባ ስለነበረ ነው፡፡

# ጥናት አስራ ሁለት ዳን 6፡1-15 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. በመንግስቱ ሁሉ ላይ እንዲገዙ አንድ መቶ ሃያ መሳፍንትን መሾም፣ በነዚህ ላይ ደግሞ ሶስት የበላይ አስተዳዳሪዎችን መሾም ሲሆን፤ ከእነዚህም ከሶስቱ መሃል ዳንኤል አንዱ ነበረ፡፡ ንጉሱ በዚህ ዓይነት ማዋቀር የፈለገው በቁ2 እንደሚታየው ንጉሱ ጉዳት እንዳይደርስበት ነው ይላል፡፡ ይህ ማለት ግብር እንደሚገባ እንዲሰበሰብ፣ ምናልባትም በአመጽ የሚነሱ እንዳይኖሩም ለመጠበቅም ጭምር ይሆናል፡፡
2. ንጉሱ ዳንኤልን በበላይነት የሾመበት ምክንያት ቁ3 ‹‹ከመሳፍንቱና ከበላይ አስተዳዳሪዎቹ ሁሉ ይልቅ ዳንኤል ልዩ የጥበብ መንፈስ የሞላበት ሆኖ በመገኘቱ፣ ንጉሱ በመላው ግዛቱ ላይ ሊሾመው አሰበ‹‹ ይለናል፡፡ የስልጣን ተዋረዱ ዳርዮስ፣ ኣንኤል፣ የበላይ አስተዳዳሪዎች፣ መሳፍንቱ…ወዘተ፡፡
3. በመጀመሪያ ክሳቸውን መመስረት የፈለጉት በሚያከናውነው ለመንግስት ሥራ ላይ ሰበብ በመፈለግ ነበረ፡፡ ዳንኤልን ለመክሰስ የሚቻልበት በቁ5 መሰረት አንድ ነገር ብቻ ሲሆን ይኸውም ከአምላኩ ህግ ጋራ በተየያዘ ብቻ ነው፡፡
4. እነዚህ ሰዎች ዳንኤል ከአምላኩ ጋራ ሳይነጋገር ለሰላሳ ቀናት መቆየት የማይችል ሰው እንደሆነ በደንብ አውቀውታል፡፡
5. እነዚህን ሰዎች ሊገልጽ የሚችለው አንድ ቃል ‹‹ቅናት›› ወይም ‹‹ምቀኝነት›› ሊሆን ይችላል፡፡ ከንጉሱ የምንመለከተው ‹‹ችኩልነት›› ‹‹አለማስተዋል›› ‹‹ሞኝነት›› የመሳሰሉት ይታዩኛል፡፡ ከባለስልጣናቱ የምማረው እግዚአብሄር ሰዎችን ሲያሳድግ አብሬ እንድደሰት እንጂ ለውድቀታቸው መልፋት ለራሴ ውድቀት እንደሚሆን ሲሆን፤ ከንጉሱ ደግሞ የምማረው በችኩልነትና አስፈላጊውን ጊዜ ሳይወስዱ ውሳኔ ማድረግ በኋላ ለጸጸት እንደሚሆን ነው፡፡
6. አዋጁ በዳንኤል መንፈሳዊ ህይወት ላይ ያስከተለው ምንም ለውጥ አላይም ‹‹ቀድሞ ያደርግ እንደነበረው ማናቸውንም ነገር ሲያደርግ እናያለን፡፡ ሰው የተከለከለውን ነገር ሲያደርግ በስውር መስኮት ዘግቶ እንጂ መስኮት ከፍቶ ንጉስ በአዋጅ የከለከለውን ነገር ማድረግ ቆራጥነቱን ያሳያል፡፡ በሮሜ 13፡1-2 ላይ ያለውን አልተላለፈም፤ ምክንያቱም ይህ ከእግዚአብሄር ህግ ጋራ የሚቃረን ህግ ስለሆነ በሃዋ ሥራ 4፡19 ላይ የተጻፈውን መመሪያ ነው ዳንኤል የተከተለው፡፡
7. ዳንኤል መሆኑን ሲያውቅ ንጉሱ አዘነ፤ ሊያድነው እንደወሰነና እስከሚመሽ ጊዜ ድረስ የተቻለውን ሁሉ እንዳደረገ እናያለን፡፡ ይህንን ሁሉ ያደረገው በዳንኤል ህይወት ከሚያየው ኑሮ ስለወደደው ነው፡፡
8. ዳንኤል ከሳሾቹን የክስ ምክንያት ያሳጣባቸው ምክንያቶች የሚለው ቁ4 እንደሚናገረው ታማኝ፣ ጠንቃቃና በሥራው እንከን የሌለበት ስለነበረ ነው ይለናል፡፡

# ጥናት አስራ ሶስት ዳን 6፡16-28 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. በዚህ ቦታ ስናነብ የዳንኤል ከሳሾች በዳንኤል ላይ ድልን እንደተቀዳጁ ይመስላል፤ ምክንያቱም በንጉሱ ትዕዛዝ መሰረት ዳንኤል ወደ አንበሶቹ አፍ ሲጣል እንመለከታለን፡፡ ንጉሱም ዳንኤልን የተሰናበተው ‹‹ሁልጊዜ የምታመልከው አምላክህ ያድንህ›› በማለት ነበረ፡፡
2. በሁለቱም ሥፍራዎች የሚታዩት አንደኛው በጉድጓዱ አፍ ላይ ድንጋይ መገጠምና፤ ሌላኛው ደግሞ በሁለቱም ላይ ማህተም መደረጉ ነው፡፡ በዚያ ሌሊት ምግብ እንዳልተበላለት፣ መዝናናትም እንዳልተቻለውና እንቅልፍም ደግሞ ከእርሱ እንደራቀ በመናገር ንጉሱ የተሰማውን ከፍተኛ ሃዘን ያሳየናል፡፡
3. ቁ19 ላይ እስኪነጋለት እንኳን ሳይጠብቅ በማለዳ መሄዱና፤ ሌላው ደግሞ አካሄዱ የጥድፊያ መሆኑ ልቡ በጣም እንደቸኮለበት ያሳየናል፡፡ ናቡከደነጾር ዳንኤል ከተጣለበት ጉድጓድ ውስጥ ገብቶ ተመልሶ በህይወት ሊወጣ የሚችል ሰው እንደሚኖር ያውቃል፤ ሆኖም በቁ20 ከሚጠይቀው ጥያቄ የእምነት ጭላንጭል በዚህ ሰው ውስጥ እንደነበረ ያሳየናል፡፡
4. ከዚህ አነጋገሩ እኔ የሚገባኝ ንጉሱ ከዳንኤል ጋራ አብዛኛውን ጊዜውን ስለሚያጠፋ አምላኩን ሲያመልክ የሚያየው በሰላም ጊዜ ወይም በተመቸው ሰዓት ብቻ እንዳልሆና በመከራም ሆነ በችግር ጊዜ ሁሉ እግዚአብሄርን ሲያመልክ የተመለከተው መሆን አለበት እላለሁ፡፡
5. በዚህ ቁጥር መሰረት ዳንኤል የህይወት ምስክርነት የነበረው በንጉሱና በእግዚአብሄርም ፊት ነው፡፡
6. ንጉሱ በቁ18 ላይ እጅግ በሃዘን ውስጥ እንደነበረ ሲታይ፤ በቁ23 ላይ ግን በደስታ ተሞልቶ እናየዋለን፡፡ ለንጉሱ ደስታ ምክንያት እንደሆነ የሚታየው ነገርም የዳንኤል ከአንበሶቹ አፍ ሳይጎዳ መውጣት መቻሉ ነበረ፡፡ እንዳይሞት ሊፈልግ የሚችልባቸው ምክንያቶች ምናልባት የዳንኤል ህይወት ስለሚማርከው፣ ወይም ህልም ፈቺ እንዳያጣ፣ ጥበብ የተሞላ ምክርን ስለሚለግሰው…ወዘተ፡፡
7. ጠላቶቹ ለዳንኤል በተዘጋጀው ነገር ውስጥ እንደገቡ እናነባለን፡፡ ነገሩን የጠነሰሱት ሰዎች ራሳቸው ብቻ ሳይሆኑ ቤተሰቦቻቸውም ጭምር ናቸው ወደ ጉድጓዱ የገቡት፡፡
8. ለእግዚአብሄር ምስጋናን አምጥቷል፡፡ ዳንኤል ለህይወቱ መሳካት የጣረውና የሞከረው አንዳችም ነገር አንመለከትም፡፡ በቁ28 ላይ የምንመለከተው ግን በነገስታቱ ሁሉ ፊት ሞገስን አግኝቶ የምድር ኑሮውም ሁሉ እንደተሳካለት እናነባለን፡፡ ከዚህ መማር የምንችለው በማቴ 6፡33 ላይ ቃሉ እንደሚናገረው አስቀድመን የእግዚአብሄርን ጽድቅና መንግስቱን ስንሻ ሌላው ሁሉ እንደሚከተል እናውቃለን፡፡

# ጥናት አስራ አራት ዳን 7፡1-28 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ቀደም ባሉት ምዕራፎች ዳንኤልን የምናውቀው እንደ ህልም ፈቺ ሲሆን፤ በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ግን ዳንኤልን የምናየው እንደ ህልመኛ ነው፡፡ በህልሙ የተመለከተው ነገር አራቱ የሰማይ ነፋሳት ታላቁን ባህር ሲያናውጡትና ከዚያም ውስጥ አራት አራዊት ከባህሩ እንደወጡ ነው፡፡ አራዊቱ በመጀመሪያ ደረጃ ታላላቅ ተብለዋል፣ እርስ በእርሳቸው እንደማይመሳሰሉ ተነግሯል፣ ከባህር ውስጥ ነው የወጡት፡፡
2. አልስማማም፤ ምክንያቱም ከፍሎቹ የሚናገሩት የሚመስል እያሉ ስለሆነ አንበሳን፣ ድብ፣ ነብር የሚመስል…ወዘተ በማለት ነው የተነገረው፡፡ ለመጀመሪያው የሰው ልብ (4) ፣ ለሁለተኛው ሥጋ (5) ለሶስተኛው ደግሞ ለመግዛት የሚያስችለወ ሥልጣን ተሰጠው፡፡
3. ይህ አውሬ የሚያስፈራ፣ የሚያስደነግጥና በጣም ሃይለኛ በማለት ይገልጸዋል፡፡ ይህንን አውሬ ከሌሎቹ ከሶስቱ የሚለየው ዋነኛ ነገር አስር ቀንዶች በእርሱ ላይ መኖራቸው ነው፡፡ ዙፋን እንደተዘረጋና ጥንታዌ ጥንቱ ተቀምጦ እያለ የተካሄደውን ነገር ነው የተመለከተው፡፡
4. ይህ አነጋገር ወደ ኢየሱስ ይጠቁመናል፤ ምክንያቱም በወንጌሎች ውስጥ ኢየሱስ ራሱን ባብዛኛው ጊዜ ‹‹የሰው ልጅ›› እያለ በመጥራት አስተዋውቆናል፡፡ ኢየሱስ ሥልጣን፣ ክብርና ታላቅ ሃይል እንደተሰጠው፤ እንዲሁም መንግሥታትና ህዝቦች ሁሉ ሲሰግዱለት እንመለከታለን፡፡
5. አራዊቱ ሁሉ ከምድር የሚነሱ መንግስታት እንደሆኑ ይነግረናል፡፡ እነዚህ ሁሉ መንግሥታት የልዑል እግዚአብሄር ቅዱሳን ለዘለዓለም እንደሚይዙት እናነባለን፡፡ ስለ አራተኛው አውሬ ትርጉም (ቁ19)፣ ስለ አስሩ ቀንዶች (ቁ20)፣ እና ስለ በኋላ ስለበቀለው ስለ አንደኛው ቀንድ ነበረ አጥብቆ ማወቅ የፈለገው፡፡
6. ቅዱሳን በጠላታቸው ሲረቱ እናያለን፡፡ ይህ የቅዱሳን መሸነፍ ልዑሉ እግዚአብሄር እስከሚመጣላቸው ጊዜ ብቻ እንደሆነ ቁ22 በግልጥ ይነግረናል፡፡
7. የተለያዩ ሰዎች የእነዚህን ጥቅሶች ሃሳብ እንዲናገሩ ጊዜ ይሰጥ፡፡ ‹‹የነገሩ ፍጻሜ ይህ ነው›› ሲል ቅዱሳን መንግስቱን እንደሚወርሱ፣ ልዕልና፣ ስልጣንና ታላቅነት ሁሉ ከእግዚአብሄር እንደሚቀበሉና፤ የእግዚአብሄር መንግሥት ደግሞ የዘለዓለም መንግሥት እንደሚሆን፣ ገዦች ሁሉ እንደሚያመልኩትና እንዲሁም እንደሚታዘዙለት በመናገር በዚህ ሁኔታ ነገሮች ይዘጋሉ ማለት ነው፡፡
8. በመንፈሱ ታወከ፣ ህልሙም እጅግ አስጨነቀው፡፡ ዳንኤል በዚህ ክፍል የተመለከተው የህልም ትርጉም ምን እንደሆነ እንዲነግረው ሲጠይቅና እርሱም ለህልሙ ትርጓሜ ሲነግረው እንመለከታለን፡፡ አንዳንዴ ለሌሎች ችግር መፍትሄን በእኛ ውስጥ ያስቀምጥና፤ የእኛን እንቆቅልሽ ደግሞ ለመፍታት በሌሎች ውስጥ በማኖር እግዚአብሄር እርስ በእርስ እንደምናስፈልግ የሚያስተምረን መንገድ ይሆናል፡፡

# ጥናት አስራ አምስት ዳን 8፡1-27 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. በምዕ 7 ያየው ንጉሱ በነገሰ በመጀመሪያው አመት ሲሆን፤ ምዕ 8 ደግሞ በሶስተኛው ዓመት ስለሆነ የሁለት ዓመት የጊዜ ርቀት ነበረ፡፡ በመጀመሪያ ያየው እንስሳ አውራ በግ ነው፡፡ ይህ በግ ሁለት ቀንዶች ነበሩት፣ ቀንዶቹ ረጃጅሞች ነበሩ፣ አንዱ ከሌላው ቀንድ ይረዝም ነበረ፣ በጉ በተለያዩ አቅጣጫዎች ይጎስም ነበረ፣ የፈለገውን ሁሉ አደረገ፣ ታላቅም ሆነ፡፡
2. ስለ አውራ በጉ እያሰበ እያለ ነው፡፡ ቀጥሎ ያየው እንስሳ አውራ ፍየል ሲሆን፤ የመጣውም ከበስተ ምዕራብ አቅጣጫ ነው፡፡
3. ፍየሉ ወደ በጉ ተንደርድሮ እንደመጣበት፣ በታለቅ ቁጣም እንደመታው፣ እንደወጋውና ሁለቱን ቀንዶቹን እንደሰበረበት፣ በጭካኔ እንደጎዳው፣ አውራ በጉ ለመቋቋም ጉልበት እንዳጣ፣ በምድር ላይ ጥሎ እንደረገጠው ይታያል፡፡ የፍየሉ ቀንድ የተሰበረው በሃይሉ በበረታ ሰዓት ነው፡፡ ትልቁ ቀንድ ሲሰበር ሌሎች አራት ታላላቅ ቀንዶች በቀሉ፡፡
4. ከአራቱ ቀንዶች መሃል በአንደኛው ላይ ሌላ ትንሽ ቀንድ ሲበቅል ይታያል፡፡ ይህ ቀንድ ከሌሎቹ የሚለየው ነገር፤ ሌሎቹ የሚዋጉት እርስ በእርስ ሲሆን፤ ይኸኛው ግን ትኩረት ያደረገው በልዑል እግዚአብሄርና በቅዱሳኑ ላይ ነው፡፡ እነዚህ ነገሮች የሚፈጸሙት፤ እስከ ሁለት ሲህ ሶስት መቶ ምሽቶችና ማለዳዎች ድረስ ይቆይና ከዚያም መቅደሱ እንደሚነጻ ቁ14 ይናገራል፡፡
5. ትርጉሙን ለዳንኤል እንዲነግረው የተጠየቀው መልዓኩ ገብርኤል ነው፡፡ ዳንኤል እንዲያስተውል የተነገረው ነገር፤ ራዕዩ ስለዘመኑ ፍጻሜ መሆኑን ሲሆን፤ በነዚህ ቁጥሮች ከምናየው በእርግጠኛነት መናገር የሚቻለው ራዕዩ ለዘመን መጨረሻ የተሰጠ እንደሆነ ነው፡፡
6. አውራ በጉ የሜዶንና የፋርስ መንግስት ነው፡፡ አውራ ፍየሉ ደግሞ የግሪክ መንግሥት ሲሆን፤ አራቱ ቀንዶች ደግሞ ከመንግሥቱ የሚነሱ አራት መንግሥታት እንደሆኑ እናነባለን፡፡
7. አስፈሪ ፊት አለው፣ አታላይ ነው፣ እጅግ ብርቱ ይሆናል፣ አሰቃቂ ጥፋት ይፈጽማል… ወዘተ፡፡ የዚህ ንጉስ ከፋት እየከፋ መሄዱን የሚጠቁመን፤ በሰዎችና በቅዱሳን ላይ ያደረገው አንሶት በልዑላን ልዑል ላይ መነሳቱ (ቁ25) የክፋቱን መጨመር ያሳየናል፡፡ ‹‹በገዛ ሃይሉ አይደለም›› ሲል የምረዳው ይህ ንጉሥ የሚያደርገውን የሚያደርገው ራሱ ሳይሆን ከበስተጓላው መንፈስ እንዳለ እመለከታለሁ፡፡
8. ያየው ራዕይ እውነት እንደሆነ መልዓኩ በቁ26 ላይ ይነግረዋል፡፡ አቅሙ ተሟጧል፣ ታሟል፣ ተኝቷል፣ ተደናግጧል፣ ነገሩም አልገባውም፡፡ ዳንኤል ከዚህ አይነት መንፈሳዊ ልምምድ በኋላ ወደ ሥራው መመለሱ መንፈሳዊነት የየእለት ተግባራችንን እንዳናከናውን የሚያግደን ነገር ሊሆን እንደማይገባ እማራለን፡፡
9. በዚህ ክፍል የተከናወነለት በእግዚአብሄርና በቅዱሳኑ ላይ ክፋትና ርኩሰትን የሚለማመድ ሰው ነው፡፡ በዚህ አነጋገር አልስማማም፤ ምክንያቱም ይህ ክፍል እንደሚነግረን የእግዚአብሄር ጠላት ሆኖ እንኳን ነገሮች ሊሰምሩልንና ሊከናወንልን እንደሚችል እንመለከታለን፡፡

# ጥናት አስራ ስድስት ዳን 9፡1-27 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. በዚህ ክፍል ዳንኤል ማቅ ለብሶ፣ በራሱም ላይ አመድ ነስንሶ፣ በጾምና በፀሎት፣ በምልጃም ወደ ጌታ አምላኩ ሲቀርብ ነው የምናየው፡፡ ለጸሎት ያነሳሳው ነገር፤ እግዚአብሄር በኤርሚያስ በኩል የገባውን የተስፋ ቃል ከመጻህፍት ስላስተዋለ ነው፡፡ ከዚህ ሰው የምማረው ቅድሚያ ለምንሰጠው ነገር ምንጊዜም ቢሆን ጊዜ እንደማናጣለት፤ ይህንንም ስናደርግ ዳንኤልን የሚከተለው የእግዚአብሄር ሞገስ እኛንም እንደሚከተለን ነው፡፡
2. እግዚአብሄር ከሚወዱትና ትዕዛዙን ከሚፈጽሙ ሁሉ ጋራ የፍቅር ቃል ኪዳኑን የሚጠብቅ እንደሆነ፣ ታላቅና የተፈራ አምላክ እንደሆነና ጌታም እንደሆነ ሲናገር፤ በሌላ በኩል ደግሞ እስራኤል ሃጥያት እንደሰራ፣ እንደበደለ፣ ክፋትን እንዳደረገ፣ እንዳመጸ፣ ከትዕዛዙና ከህጉ ዘወር እንዳሉ… ነብያቱንም እንዳልሰሙ ይናገራል፡፡
3. ምንም እንኳን ዳንኤል በቤተ መንግሥት ውስጥ የሚኖር ቢሆን የእርሱ ልብ ዘወትር ከህዝቡና ከፈረሰችው ከኢየሩሳሌም ተለይቶ ስለማያውቅ በሥጋው በቤተ መንግስት ውስጥ ይሁን እንጂ ራሱን ከህዝቡ ጋራ ስለሚያይ የህዝቡ ሃፍረት የእርሱም ሃፍረት፣ ውድቀታቸውም ውድቀቱ ነበረ፡፡
4. በህዝቡና በኢየሩሳሌም ላይ ለደረሰው ነገር ተጠያቂ የሚያደርገው ራሱንና ህዝቡን በሙሉ ነው፡፡ እግዚአብሄር ጻድቅ፣ ይቅር ባይና መሃሪ እንደሆነ ይጠቁመናል፡፡
5. የመጀመሪያው ከሃጥያት መመለስ ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ እውነትን መከተል ወይም በጽድቅ መንገድ መራመድ ናቸው፡፡ እግዚአብሄር የወሰዳቸው እርምጃዎች የእርሱን ጻድቅነት የሚያረጋግጡ ሆነው ነው የቀረቡት፡፡
6. ገብርኤል ሲመጣ ዳንኤል እየተናገረ፣ እየጸለየ፣ የራሱንና የህዝቡን ሃጥያት እየተናዘዘ፣ ስለቅዱሱ ተራራው እግዚአብሄርን እየለመነና እየጸለየ ነበረ፡፡ መልዓኩ የመጣው ለዳንኤል ጥበብንና ማስተዋልን ለመስጠት፣ እንዲሁም ገና ዳንኤል መጸለይ ሲጀምር ለጸሎቱ መልስ እንደተሰጠ ሊነግረው እንደመጣ ነው የነገረው፡፡ ዳንኤል ከገብርኤል የተቀበላቸው ሁለት ምክሮች፤ የመጀመሪያው መልእክቱን ልብ እንዲልና፣ ሁለተኛው ደግሞ ራዕዩን እንዲያስተውል ናቸው፡፡
7. ዳንኤል መጸለይ የጀመረው እግዚአብሄር በኤር 25፡11-12 የተናገረው ሰባ ዓመት ስለደረሰ ኢየሩሳሌምንና ህዝቡን እንዲጎበኝ ነበረ፡፡ በቁ24 ላይ ግን እግዚአብሄር ወደ አገራቸው የመመለስን ብቻ ሳይሆን አጠቃላይ ሊሆን ያለውን ክርስቶስ እስከሚመጣ ድረስ ያልጠየቀውን ሁሉ መለሰለት፡፡ ከምናስበውና ከምንለምነው በላይ ያደርጋል የሚለውን በዳንኤል ሲፈጽም እንመለከታለን፤ እኛም በቃሉ ላይ ተመስርተን እንድንጸልይ ይህ ማበረታቻ ሊሆነን ይገባል፡፡
8. አመጻን ለማስቆም፣ ሃጥያትን ለማስወገድ፣ በደልን ለማስተሰረይ፣ ዘላለማዊ ጽድቅን ለማምጣት፣ ራዕይንና ትንቢትን ለማተም፣ እጅግ ቅዱስ የሆነውን ለመቀባት፡፡ ቁ25 የሚያወራው ስለኢየሩሳሌም ቅጥር ማደስና መጠገን ስለሆነ የአዋጁ መጀመሪያ እንደሆነ የምለው በነህምያ 2፡5 የተነገረውን ነው እላለሁ፡፡
9. እያገለገለ ያለው የተለያዩ መንግስታትን ነው፡፡ ራሱን በቁ17 የሚያስተዋውቀው እንደ እግዚአብሄር አገልጋይ አድርጎ ነው፡፡

# ጥናት አስራ ሰባት ዳን 10፡1-11፡1 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. የፋርስ ንጉስ ቂሮስ በነገሰ በሶስተኛው ዓመት ነው። የታየው ራዕይ ታላቅ ጦርነትን አስመልክቶ ሲሆን፤ መልዕክቱ ደግሞ እውነተኛነቱ በዚህ ክፍል ተረጋግጧል።
2. ለሶስት ሳምንት አለቀሰ፣ ሶስቱ ሳምንት እስኪፈጸም ድረስ ምርጥ ምግብ አልበላም፣ ሥጋም ሆነ የወይን ጠጅ ወደ አፉ አላስገባም፣ ቅባትም አልተቀባም። ይህ ዳንኤል ያየው ሰው በፍታ የለበሰ፣ ምርጥ የወርቅ ቀበቶ የታጠቀ፣ አካ እንደ ዕንቁ፣ ፊቱ እንደመብረቅ፣ ዓይኖቹ እንደሚንበለበል ፋና፣ ክንኮቹና እግሮቹ እንደጋለ ናስ የሚያብረቀርቁና ድምፁ እንደ ብዙ ህዝብ ድምጽ እንደነበረ እናነባለን።
3. ራዕዩን ማየት ሲጀምር ሰዎች ከእርሱ ጋራ እንደነበሩ ቁ7 ሲያረጋግጥልን፣ ራዕዩ ግን ይታይ የነበረው ለእርሱ ብቻ እንደነበረ በዚያው ቁጥር ውስጥ ማየት እንችላለን። እነዚህ ቁጥሮች የሚያስታውሱኝ በሐዋ ሥራ 9:3-7 ያለው ጳውሎስን ጌታ የሱስ የተገናኘበት ጊዜ ያስታውሰኛል።
4. ለዳንኤል የተሰጠው ስያሜ ‹‹እጅግ የተወደድህ›› የሚል ነበረ። ይህ ስያሜ እኔ ሲገባኝ መላዕኩ ደጋግሞ ይናረው እንጂ፤ በተለይ በ9፡23 ላይ ስናይ ከጸሎቱ መሰማት ጋራ አያይዞ ስለተናገረ በእግዚአብሄር እጅግ መወደዱን የሚገልጽ ሆኖ ነው የማየው።
5. ማስተዋልን ለማግኘትና፣ በአምላኩ ፊት ራሱን ለማዋረድ ነበረ ዳንኤል የወሰነው። ቁ12 እንደሚናገረው ጸሎት በጀመረ በመጀመሪያው ቀን የተመለሰለት ሲሆን፤ ለእርሱ የደረሰው ግን ከሶስት ሳምንት በኋላ ነው። ቁ3 ላይ እንደምናነበው ሶስቱን ሳምንት ሁሉ በጾምና ጸሎት ላይ ነበረ። ይህ የሚያስተምረኝ፤ የዳንኤልን ጸሎጵ ማዘግየት ከቻለ የእኔም ጠላት ስለሆነ የእኔንም የጸሎት መልስ ሊያዘገይ እንደሚችልና እኔም መልሴ እስኪመልኝ ድረስ በትጋት በእግዚአብሄር ፊት መቆየት እንደሚኖርብኝ እማራለሁ።
6. የመጀመሪያው ራዕዩ ለመፈጸም ገና ብዙ ዘመን የሚቀረው እንደሆነና፤ ሁለተኛው ደግሞ ራዕዩ በዳንኤል ህዝብ ማለትም በእስራኤላውያን ላይ ያተኮረ ነው። እኔ እንደሚመስለኝ ዳንኤል ህዝቤ ሰባ የግዞት ዓመቱን ጨረሰ ብሎ ደስ በሚሰኝበት ሰዓት ይህ በቁ1 ላይ ‹‹ታላቅ ጦርነት›› የተባለው ውስጥ እንደገና መግባታቸው ታላቅ ሃዘንና ስብራት የለቀቀበት ሆኖ ነው የሚታየኝ።
7. ሰው የሚመስለው ዳስሶት ካበረታው በኋላ ነው እንደገና በርትቶ ለመስማት የተዘጋጀው። መልዕክተኛው ከመሄዱ በፊት ለዳንኤል ሊነግር የፈለገው በእውነት መጽሃፍ ውስጥ የተጻፋን ነገር ነው።
8. ኢየሱስ ነው የሚሉት በቁ4-6 ላይ ያለው በራዕይ 1:13-16 ላይ ካለው ስለሚመሳሰል፣ ቁ7 ላይ በሰዎቹ ላይ የሆነው ነገርና፣ ሌላ ደግሞ ‹‹ሰው›› እያለ ሚናገረው በዳን 7፡13 ላይ የሰው ልጅ የሚለውን ሊሆን ይችላል ሲሉ እኔ ግን ኢየሱስ ወዳንተ ተልኬአለሁ ቁ11 የፋርስ መንግስት አለቃ ‹‹ተቋቋመኝ›› ፣ ‹‹ሚካኤል ሊረዳኝ መጣ›› የሚሉት አነጋገሮች ከኢየሱስ ማንነት ጋራ ስለማይሄዱ ኢየሱስ ነው ብዬ አላምንም።
9. በቅዱሳን መላዕክትና በርኩሳን መናፍስት መካከል የሚደረገውን ጦርነት ነው የምናየው። መልአኩ ለዳንኤል የጸሎቱን መልስ ማድረስ የቻለው በሚካኤል እርዳታ ጭምር መሆኑ ይታያል።

# ጥናት አስራ ስምንት ዳን 11፡2-35 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. አራት ነገስታት እንደሚነሱ ነው የተናገረው፡፡ አራተኛው ንጉስ ከሁሉ ይልቅ እጅግ ባለጠጋ እንደሚሆን፣ በባለጠግነቱም እጅግ እንደሚበረታ፣ ለሎችን አሳድሞ በግሪክ መንግስት ላይ እንደሚነሳ እናነባለን፡፡
2. ይህ ንጉስ በፋርስ ላይ የሚነግስ ነው ብዬ አላምንም፤ ምክንያቱም መልአኩ ለዳንኤል የነገረው ከዳርዮስ በኋላ አራት ነገስታት እንደሚነግሱ ብቻ ነው፡፡ ይህ በታላቅ ሃይል የሚገዛ ተብሎ የተነገረለት ከታሪክም እንደሚረጋገጠው የግሪክ ንገስ የነበረው አሌክሳንደር ዘግሬት በመባል የታወቀው ሰው ነው፡፡ በቁ4 ላይም አሌክሳንደር በ32 ዓመቱ ሞቶ መንግስቱን ለልጆቹ ሳይተላለፍ አራት ጀነራሎቹ እንደተከፋፈሉት ሲያሳይ ታሪክም ይህንኑ ያረጋግጣል፡፡
3. በነዚህ ቁጥሮች ውስጥ በብዛት የተጠቀሱት ሁለቱ ቃላት የሰሜን ንጉስና (ሶርያ)፣ የደቡብ ንጉስ (ግብጽ) የሚሉት ናቸው፡፡ ይህ የተባለለት በቁ15 ላይ የምናነበው የሰሜኑ ንጉስ በመባል የታወቀው የሶርያ ንጉስ ነው፡፡
4. የተናቀ ሰው እንደሚሆን፣ ንጉሳዊ ክብር እንደማይሰጠው፣ በተንኮል መንግስቱን እንደሚይዝ ይታያል፡፡ ይህ ሰው የሚያደርጋቸው ደግሞ፤ የቃል ኪዳኑንም አለቃ ሳይቀር ይደመስሳል፣ የማታለል ሥራውን ይሰራል፣ ከጥቂቶች ጋራ ለስልጣን ይበቃል፣ የበለጸጉትን አገሮች በድንገት ይወራል፣ አባቶቹም ሆኑ አያቶቹ ያላደረጉትን ሁሉ ያደርጋል… ወዘተ፡፡
5. የግብጹ ንጉስ የተሸነፈበት ምክንያት ቁ25 ከተዶለተበት ሴራ የተነሳ እንደሆነ ይነግረናል፡፡ እነዚህ ነገስታት ልባቸው ለክፋት ያዘነበለ ሆኖ እያለ በአንድ ገበታ አብረው እየበሉ እርስ በእርሳቸውም ሃሰት ይነጋገራሉ፡፡
6. የሰሜኑ ንጉስ ወደ አገሩ ሲመለስ እግረ መንገዱን በተቀደሰው ኪዳን ላይ እንደሚነሳና ክፉ ነገርም እንደሚያደርግ ቁ28 ይነግረናል፡፡ ተመልሶ ደቡቡን ለማጥቃት ሲመጣ የኪቲም መርከቦች እንደ ተቃወሙትና ልቡም እንደተሸበረ እናነባለን፡፡ በሽንፈቱ የተሰማውን ቁጣ በተቀደሰው ኪዳን ላይ ያወርዳል፤ የተቀደሰውን ኪዳን የተውትን ይንከባከባል፡፡
7. የጦር ሰራዊቶቹ ቤተ መቅደሱንና ቅጥሩን ያረክሳሉ፣ የዘወትሩን መስዋዕት ያስቀራሉ፣ ጥፋትን የሚያመጣውን የጥፋት ርኩሰት ይተክላሉ፣ ኪዳኑን የሚተላለፉትን በማታለል ያስታል፡፡ ይህ ክፍል ጸንተው የሚቃወሙትን ሰዎች ‹‹አምላካቸውን የሚያውቁ ህዝብ›› ይላቸዋል፡፡
8. ሊደርስባቸው የሚችሉት ነገሮች፤ በሰይፍ መውደቅ፣ መቃጠል፣ መማረክ፣ መዘረፍ ናቸው፡፡ ከተማሪዎቻቸው መሃል እውነተኛ ያልሆኑ አስመሳይ ብዙ ሰዎች እንደሚገኙባቸው እናነባለን፡፡
9. እነዚህን ሰዎች የረዳቸው አንድ ነገር ቢኖር እግዚአብሄርን ማወቃቸው ነበረ፡፡

# ጥናት አስራ ዘጠኝ ዳን 11፡36-12፡3 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. የመጨረሻውን ዘመን የሚጠቁም ይመስለኛል፤ ምክንያቱም በቁ40 ላይ ‹‹በመጨረሻው ዘመን›› በ12፡1 ‹‹በዚያን ጊዜ ስማቸው በመጽሐፍ ተጽፎ የተገኘው…›› በ12፡2 ‹‹…አንዳንዶች ለለዘላለም ህይወት፣ ሌሎችም ለውርደትና ለዘላለም ጉስቁልና ይነሳሉ፤፤›› የሚሉት ሃሳቦች በዘመን ፍጻሜ ላይ ያተኮረ ትንቢት እንደሆነ ይጠቁሙናል፡፡
2. ይህ ንጉስ ደስ እንዳለው ያደርጋል፣ ከአማልክት ሁሉ በላይ ራሱን እጅግ ከፍ ያደርጋል፣ በአማልክት አምላክ ላይ ተሰምቶ የማይታወቅ የስድብ ቃልን ይናገራል፡፡ ይህ ሁሉ እንዲሆን እግዚአብሄር ስለፈቀደበት ምክንያት በዚሁ ቁጥር ውስጥ እንደምናነበው፤ የቁጣው ዘመን እስኪፈጸምና እግዚአብሄር ራሱ የወሰነው ነገር ሁሉ መሆን ስላለበት ነው፡፡
3. ይህ ሰው ለብዙዎች ነገሥታትንም ሆነ ታላላቅ ሰዎች ውድቀት የሚሆኑት ለሴቶች ግድ የለውም፣ ለአባቶቹም አምላክ ግድ የለውም፣ ማንኛውንም አምላክ አያከብርም፣ ራሱን ከማናቸውም ነገሮች በላይ ከፍ ከፍ ያደርጋል፣ የምሽጎችን አምላክ እንደሚያከብር፣ በወርቅ፣ በብር፣ በከበሩ ድንጋዮችና በውድ ስጦታዎች ያከብራል፡፡ ይህ ማለት የሚመስለኝ ንጉሱ በጦር ሃይልና በምድራዊ ሃብት ይተማመናል፡፡
4. ጽኑ ምሽጎችን ለመውጋት ሃይሉን የሚያገኘው በባዕድ አምላክ እርዳታ ነው ይለናል፡፡ በ2ኛ ተሰ 2፡9 ሃሰተኛው ክርስቶስ በሰጥጣን ሃይል እንደሚሰራ የተነገረው እንደሆነ ይመስለኛል፡፡ ለእርሱ ለሚገዙት እጅግ ያከብራቸዋል፣ በብዙ ህዝብ ላይ ገዥዎች ያደርጋቸዋል፣ ምድሩንም በዋጋ ያከፋፍላቸዋል፡፡
5. ይህ ክፍል ስለ መጨረሻው ዘመን እንደሚናገር ቁ40 ግልጽ አድርጎ አስፍሮታል፡፡ ‹‹መልካሚቱ ምድር›› ሲል የእርራኤልን ምድር እንደሆነ ነው የምረዳው፡፡
6. ይህንን ንጉስ የሚያስደነግጠው ነገር ከምስራቅና ከሰሚን የሚመጣው ወሬ ነው፡፡ የዚህ ሰው መጨረሻ በተመለከተ ቁ45 እንደሚናገረን ወደ ፍጻሜው እንደሚመጣና፤ ማንም እንደማይረዳው እናነባለን፡፡
7. ስለ ዳንኤል ህዝብ ማለትም ስለ እስራኤል የሚቆመው ሚካኤል ይነሳል፤ ታላቅ የመከራ ጊዜ ይሆናል (ማቴ 24፡21) ፣ ስማቸው በመጽሃፍ ተጽፎ የተገኘው እስራኤላዊ ሁሉ ይድናል፡፡ እነዚህ ነገሮች የሚሆኑት ‹‹ህዝብህ›› በማለት የሚናገራቸው የእስራኤል ህዝብ ነው፡፡
8. የሞቱ ሰዎች እንደሚነሱ፣ አንዳንዶች ለዘለዓለም ህይወት፤ አንዳንዶች ደግሞ ለዘለዓለም ጉስቁልና እንደሚነሱ እንማራለን፡፡ ቁ2 ሰዎች እጣ ክፍላቸው የዘለዓለም ህይወት ወይም የዘለዓለም ጉስቁልና ሊሆን እንደሚችል ሲነግረን፤ ቁ3 ደግሞ የሰዎቹን የዘለዓለም አድራሻ የመቀየርና ወደ ጽድቅ የመመለስ ነገር በሰዎች ጫንቃ ላይ እንዳለ ያረጋግጥልናል፡፡ ብዙዎችን ወደ ጽድቅ የሚመልሱ እንደ ከዋክብት ለዘላለም እንደሚደምቁ ቃል ተገብቶላቸዋል፡፡

# ጥናት ሃያ 12፡4-13 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ቁ4 ያተኮረው በዳንኤል በራሱ ላይ ነው፡፡ ዳንኤል የታዘዛቸው ሁለት ትዕዛዞች እስከ ፍጻሜው ዘመን ድረስ የመጽሃፉን ቃል እንዲዘጋና፤ እንዲያትመው ነው፡፡ እነዚህ የሚሆኑት ነገሮች፡ የመጀመሪያው ብዙዎች ወዲያ ወዲህ እንደሚራወጡና፤ ሌላው ደግሞ እውቀት እንደሚበዛ ነው፡፡
2. ዳንኤል፣ ሌሎች ሁለት ምናልባትም መላዕክት ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ የተጠየቀው ጥያቄ ‹‹እነዚህ አስደናቂ ነገሮች ሊፈጸሙ ምን ያህል ጊዜ ይቀራል?›› የሚል ነበረ፡፡ መልሱ ‹‹ለዘመን፣ ለዘመናት፣ ለዘመን እኩሌታ ይሆናል›› የሚል ነው፡፡
3. ዳንኤል በቁ8 ላይ እንደምናየው የተናገሩት ነገር ሊገባው እንዳልቻለ እናያለን፡፡ ዳንኤል የጠየቀው ጥያቄ ‹‹የዚህ ሁሉ ፍጻሜ ምንድነው?›› የሚል ሲሆን፤ እኔ ሲገባኝ ዳንኤል የጠበቀውን አይነት መልስ ያገኘ አይመስለኝም፤ ምክንያቱም እርሱ ማወቅ የፈለገው አንድ ማጠቃለያ የሆነ ሃሳብ እንዲነገረው የፈለገ ይመስለኛል፤ ሆኖም መልአኩ የመለሰለት ነገሮቹ የተዘጉና የታተሙ ስለሆኑ አያስጨንቅህ የሚለው ነው የሚመስለኝ፡፡
4. ታተመና ተዘጋ ሲል ልክ ማቴ 24፡15 ላይ እንደምንመለከተው የትንቢቱ ቃል ሙሉ መረዳት ሊኖር የሚችለው ‹‹የፍጻሜ ዘመን›› በመባል በተነገረው ሰዓት ላይ መሆኑን የሚያሳይ ሲሆን፤ ዳንኤልም እንኳን ያየውን፣ የሰማውንና የጻፈውን ሙሉ በሙሉ መረዳት እንዳልቻለ እንመለከታለን፡፡
5. ለዮሃንስ የተሰጠው ትዕዛዝ የትንቢቱን ቃል በማህተም እንዳይዘጋው ሲሆን ምክንያት ተደርጎ የተሰጠውም ‹‹ጊዜው ስለደረሰ›› የሚል ነው፡፡ ዮሃንስ እንዳይዘጋው ሲነገረው፤ ዳንኤል ግን እስከ ፍጻሜው ዘመን ድረስ እንዲዘጋው ተነግሮታል፡፡
6. ክፉዎችና ጠቢባን በማለት ይከፍላቸዋል፡፡ ብዙዎች እያለ የሚጠራቸው ጠቢባኑ ያስተውላሉ፣ ይጠራሉ፣ ይነጻሉ፣ እንከን አልባም ይሆናሉ፤ በሌላ በኩል ደግሞ ክፉዎች የሚላቸው አንዳቸውም አያስተውሉም፣ በክፋታቸውም ይጸናሉ፡፡
7. ሁለቱ ሃሳቦች፤ የዘወትሩ መስዋዕት መቋረጥና ጥፋት የሚያመጣው ርኩሰት መተከል ናቸው፡፡ መስዋዕት የመሰዋት ስርዓት ቤተ መቅደስ ስለሌለ ሊካሄድ አይችልም፤ ስለዚህም እነዚህ ነገሮች እንዲከናወኑ ካስፈለገ አስቀድሞ ቤተ መቅደስ ሊገነባ ያስፈልጋል ማለት ነው፡፡
8. ስለራሱ የተነገሩት ነገሮች፤ እስከ ፍጻሜው ድረስ እንዲሄድ፣ እንደሚያርፍ ማለትም እንደሚሞት፣ በቀኖቹ መጨረሻም እንደሚነሳ፣ የተመደበለትን ርስት እንደሚቀበል የሚሉት ናቸው፡፡